ethnic communities' council of victoria

በቪክቶሪያ ካሉት የጎሳና መድብለ ባህላዊ ድርጅቶች ውስጥ የቪክቶሪያ ጎሳ ማህበረሰብ መማክርት ማሕበር (ECCV) ከፍተኛው አካል ነው። ይህ በማህበረሰባት የተመሰረት ሲሆን ከተለያየ አገር ለመጡ ሰዎች ለማጠናከር የድርጅት መሪ አባላት መስዋእትነት ነው። ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ በቪክቶሪያ ውስጥ በባህላዊ ልዩነት ላላቸው ማህበረሰባት ዋና ደጋፊ በመሆናችን እንኮራለን። በመድብለ ባህላዊ ማህበረሰባት፣ በመንግሥትና ሰፋ ባለ ማህበረሰብ መካከል ከ35 ዓመት በላይ ግንኙነት እንፈጥር እንደነበር ነው።

ለድርጅቱ የሚወክል፣ ጠበቃ የሚሆን፣ ፖሊሲ የሚያወጣ እና የማሻሻል አቅም ያለው በሊቀመንበር የሚመራ በፈቃደኝነት የተመሰረተ ቦርድ እና የሙሉ ቀን የሙያ ሠራተኞች አሉን። በማንኛውም የመንግሥት ደረጃ ላሉ የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰባት ፍላጎት ማለት እንደ ሰብዓዊ መብቶች፣ አቅርቦትና ትክክለኛ ፍትሕ፣ አገልግሎትን ስለማሻሻል፣ ዘረኝነትና አድልዎ መፍጠር፣ የማህበረሰብ ውህደት፣ ሥራና ሠራተኛ፣ ትምህርትና ስልጠና፣ ጤንነትና የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የአካል ጉዳተኛ፣ የህጻን መከላከያ፣ ህግና ፍትሕ እንዲሁም ስነ-ጥበብና ባህል በተመለከተ ፍላጎት ላይ ድርጅቱ ተጠሪ ይሆናል። ለአባሎቻችን በሚያሳስብ ማንኛውም ጉዳይ ላይ ጥብቅና እንቆማለን እንዲሁም ከአብዛኛው የሶስተኛ ትምህርት ተቋማት በጋራ አብረን ሰፋ ባሉ ጉዳዮች ላይ በጽሁፍ የፖሊሲ ወረቀቶችን በማውጣት አንዳንዴም የምርምር ጥናት እናካሂዳለን።

እንዲሁም የእኛ ድርጅቶች አባል ለሆኑ እና ከአዲስና ብቅብቅ ከሚሉ ማህበረሰባት ለተውጣጡ አባላት የአቅም ግንባታ ለማዳበር የአመራር ስልጠና በማቅረብ እንረዳለን።

የእኛ አባልነት መሆን ሰፋ እና በተለያየ ሁኔታ የተመሰረተ ነው። ከጎሳ ወይም ከመድብለ ባህላዊ ጋር ባተኮረ፣ በነዚህ መስኮች ላይ ፍላጎት ላላቸው ድርጅቶች ግልጽ ሲሆን፣ ወይም እኛ የምናካሂደውን ሥራ ለሚደግፉ ግለሰቦች ግልጽ ነው። እኛ ስለምናካሂደው ነገሮች ሁሉ ለማግኘት በእኛ ድረገፅ ላይ መፈለግ ሲሆን በ ECCV ላይ ለመሳተፍ ማመልከቻ በዚህ ድረገፅ "*Become a Member*" in "*About*" ወደሚለው መሄድ። ስለምናካሂደው ነገሮች ሁሉ ለማወቅና እንዴት አድርገን የማህበረሰብዎን ከፍተኛ ስሜት መርዳት እንደምንችል ለማወቅ በስልክ ደውለው እንዲጠይቁን ተጋብዘዋል።

አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ እባክዎ ለትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (TIS National) በስልክ **131 450** ይደውሉና ከዚያም በቪክቶሪያ የጎሳ ማህበረሰባት መማክርት ማሕበር (ECCV) በስልክ (03) 9349 4122 ደውለው እንዲያገናኝዎ ይጠይቋቸው። የእኛ ሥራ ሰዓታት ጥዋት 9.00am እስከ ከሰዓት በኋላ 5.00pm፤ ከሰኞ እስከ ዓርብ ይሆናል።


**Ethnic Communities' Council of Victoria**
150 Palmerston Street Carlton VIC 3053
**ስልክ:** 9349 4122
**ፋክስ:** 9349 4967
www.eccv.org.au